# የህዝባዊ እምቢተኛነት የነጻነት ትግል በፖለቲካ ድርጅቶች የመመካከርና የመተባበር አጀንዳ ላይ ያሳደረው ተጽእኖ

## 1. የወቅቱ የትብብር ጥሪ ልዩ ገጽታዎች

የሃገራችን የፖለቲካ ድርጅቶች "እንሰባሰብ፣ እንቀናጅ፣ ትብብር እንፍጠር" በማለት መድከማቸውን እናውቃለን። እስካሁን የድካማቸው ውጤት ግን ፍሬ አፍርቶ አልታየም። ትብብሩ ያልተሳካበት ምክንያት ብዙ ነው። እያንዳንዱ ድርጅትም ያልተሳካበትን ምክንያት በራሱ መነጽር እንደሚያየው ይታወቃል። እነዚህን ምክንያቶች መዘርዘር የዚህ ጸሁፍ አላማ አይደለም። አሁንም ቢሆን ይህ የመተባበር ጥያቄ አንገብጋቢ ነው። ዛሬ ተገንብቶ ነገ የሚፈርስ ሳይሆን በከፍተኛ የህዝብ ወገንተኛነት፣ የሃገር ተቆርቋሪነት ላይ የተመሰረተ በድርጅቶች መካከል የሚታዩ ችግሮችን ብቻ ሳይሆን የማህበረሰባችንን የተወሳሰቡ ችግሮች ለመፍታት አልሞ የተነሳ ስትራቴጂያዊ ግብ ያለው የሁሉም ድርጅቶች ትብብር እንደሚያስፈልገን አጠያያቂ አይደለም። በዚህም ምክንያት የግንቦት 7 ንቅናቄ ከተለያዩ ድርጅቶች ጋር ጠንካራ ትብብር ለመፍጠር የጀመረውን ጥረት አጠናክሮ ይቀጥላል።

የዚህ ጽሁፍ አላማ ከላይ የተጠቀሰውንና ብዙ ስራ የሚጠይቀውን፤ የኢትዮጵያ ህዝብ መብቱ፣ ነጻነቱ፣ አንድነቱ እንዲከበር ሰላሙ እንዲረጋገጥ፤ በርጋታ ፊቱን ወደ ልማት አዙሮ የሰውና የተፈጥሮ ሃብቱን በሚገባ በመጠቀም አዋራጅ ከሆነው ድህነት እንዲላቀቅ አስፈላጊ የሆነው የሃገሪቱ የፖለቲካ ድርጅቶች ትብብር አስፈላጊነት ወደ ጎን ያደረገ አይደለም። ይህ ጽሁፍ ያተኮረው ከዚህ ቀደም ስለትብብር ስንመካከር በአካባቢያችን ያልነበረው የቱኒዝያና የግብጽ ህዘባዊ እምቢተኛነት አዲስ ታሪካዊ ክስተት በፖለቲካ ድርጅቶች የመተባበር ጥያቄ ላይ ይዟቸው የመጣቸውን ያልተጠበቁ ጫናዎች ለመፈተሽ ነው።

ከሰሜን አፍሪካና መካከለኛው ምሥራቅ ህዝባዊ አብዮቶች በኋላ እየተነሳ ያለው የእንነጋገር፣ የእንመካከር እና የእንተባበር ጥያቄ ካለፉት የመተባበር ጥያቄዎች የተለየ ነው። የአሁኑ ጥያቄ መነሻው የድርጅት መሪዎችና የአባላቶቻቸው ፍላጎት አይደለም። ይህን ማለት ግን ድርጅቶችና አባላቶቻቸው በሰሜን አፍሪካ ህዝብ ታሪክ ሰሪነት አልተነኩም ለማለት አይደለም። የወቅቱ የትብብር አስፈላጊነት ጥሪ በቱኒዝያና በግብጽ የታየው ህዝባዊ እምቢተኛነት በመላው ህብረተሰባችን በተለይ ከፖለቲካ ልሂቁ ወጭ ባለው ህብረተሰብ ላይ ያሳደረው ተጽእኖ ነው።

የሰሜን አፍሪቃው ህዝባዊ እምቢተኛነት የተቃዋሚ ድርጅቶችን መሪነት አልፈለገም። በተመሳሳይም የድርጅቶችን መሪነት የማይጠብቅ ህዝባዊ አመጽ በኢትዮጵያ ይነሳል የሚል ግምት አለ። ስለዚህም የአሁኑ "እንጋገር፣ እንመካከር" አይቀርም ተብሎ የሚጠበቀውን የሃገራችን ህዝባዊ ቁጣ እሳቤው ያደረገ ነው።

የሚከተሉት ጥያቄዎች እየተነሱ ነው።

- የቱኒዚያና የግብጽ አይነቱ ህዝባዊ አመጽ ኢትዮጵያ ውስጥ ሲነሳ ምን ማድረግ ይገባናል?
- ህዝቡ ለራሱና ለተቃዋሚ ድርጅቶች በነጻ የመንቀሳቀስ መብት የሞት የሽረት ትግል ወደሚያደርግበት ሁኔታ እየገባ ነው። በዚህ ወቅት ህዝብን ነጻ እናወጣለን ብለው የተደራጁ ሃይሎች ነጻ ሊያወጣቸው የተነሳውን ህዝብ ዝም ብለው ሊያዩት ነወይ?
- በግብጽና በቱኒዝያ ህዝባዊ አብዮት ምክንያት ታግደው የነበሩ፤ ተሰደው የነበሩ፤ ተቀብረው የነበሩ ድርጅቶችን ነጻ አውጥቷል። በኛስ ሃገር ይህ የማይሆንበት ምክንያት ይኖራልን?

- ከዚህ ቀደም በጋራ እንስራ እንተባበር የሚሉ ጥረቶቻችን አልተሳኩምና አሁንም ምንም ነገር ማድረግ አንችልም ብለን እንቀመጥ ወይ?
- ህዝብን እኛ ተቃዋሚዎች ልዩነቶቻችንን አስወግደን ትብብር አልፈጠርንምና መነሳትንህን አቁም እንበለው? ብንለውስ እሺ ብሎ ያቆማል ወይ? ይህስ አቋም በታሪክ የሚያስጠይቅ አይሆንም ወይ?

ከላይ ለተዘረዘሩት ጥያቄዎች በሚሰጧቸው መልሶች አብዛኛኖዎቹ ድርጅቶች ይስማማሉ ብለን እናስባለን።

የምክክር አስፈላጊነትና አጣዳፊነት በሁሉም ጸረ- አምባገነናዊነት ሃይሎች ተቀባይነት ይኖረዋል ብለን እንድናምን ያደረጉን ተጨማሪ እሳቤዎች አሉ። የኢትዮጵያ ህዝብ ስለቱኒዝያና የግብጽ ወጣትና ማህበረሰብ ክንውኖች የሚያሳየውን አድናቆትና አክብሮት ለዴሞክራሲያዊ ስርአት መመስረት የቆሙ የኢትዮጵያ የፖለቲካ ድርጅቶችና የሲቪል ማህበራት ሁሉ ይጋራሉ። እነዚህ ሃይሎች በግብጽና በቱኒዝያ የታየው ተመሳሳይ ሁኔታ በሃገራችን ቢፈጠር እጅግ ይደሰታሉ። ተቃዋሚዎች እራሳቸው ተሰባስበውና ተጠናክረው ማምጣት ያልቻሉትን ለውጥ ህዝብ ባጭር ጊዜ ማምጣት መቻሉ እርካታ የሚሰጣቸው ይሆናል። ባለንበት ወቅት "እኔ ካልመራሁት ህዝብ መነሳት የለበትም፤ እኔ ያልመራሁት ለውጥ መምጣት አይገባውም" ብለው የሚያስቡ ድርጅቶች አይኖሩም። "ህዝብ ቢያምጽና አመጹም ለዴሞክራሲያዊ ስርአት ምስረታ እስከሆነ ድረስ ሁሉም ድርጅቶች አመጹ ለማቀጣጠል የሚባትለውን ህዝብ እንዴት እናበረታተው? እንዴት እንደግፈው?" በሚል ጉዳይ ላይ ለመመካከር ጥሪ ብናደርግ ተቃውሞ አይኖራቸውም የሚሉት እሳቤዎች ግንቦት 7 ንቅናቄን ለምክክሩ ተግቶ እንዲሰራ አድርገውታል።

በእነዚህ እሳቤዎችት ትክክለኛነት ላይ ተማምነን የግንቦት7ና የጥምረት ለፍትህ ለነጻነትና ለእኩልነት አባል ድርጅቶች አመራር አካላት ከሁሉም የነጻነት ግንባሮች፣ የተቃዋሚ የፖለቲካ ድርጅቶች፣ የሲቪክ ማህበራት ጋር ለመመካከር ሞክረናል። በኛ በኩል የቱኒዝያና የግብጽ አብዮቶች የከፈቱልን የጸረ-አምባገነንነት የትግል አግባብ እርስ በርሳችን ለመነጋገሪያ የሚሆን አጣዳፊና ተጨባጭ የምክክር አጀንዳ ይዞልን መጥቷል የሚል እምነት አለን። በመሆኑም ድርጅቶችን በተናጠልም ይሁን በጋራ፤ ትንሽ ትልቅ ሳንል፤ በኢትዮጵያ ውስጥ ሊቀሰቀስ ስለሚችለው የህዝባዊ እምቢተናኛነት አመጽና የተቃዋሚ ድርጅቶች ሚና ጉዳይ ላይ ለማማከር ጥረት አድርገናል። ይህን ጥረታችንን እንድንቀጥልበትና ብሎም ወደላቀ የምክክርና የትብብር ደረጃ እንዲሚያደግ ተስፋ እንድንሰንቅ የሚያደረግ አበረታታች ሁኔታዎች እያየንበት ነው። ይህ ጽሁፍ በአዲሱ የትብብር ምንነት ዙሪያ አሉ ብለን የምናስባቸውን ውዥንብሮችና ሌሎችንም የመተባባር ጥረታችን ደንቃራ የሆኑ ጉዳዮችን የምናጠራበት ነው።

## 2. ትንሽ እገዛ ብቻ የሚሻ ህዝብና የምክክር አስፈላጊነት

የሃገራችን ህዝብ በግብጽና በቱኒዝያ ወንድምና እህቶቹ ክንውኖች ተነቃቅቷል። ከዚህ በተጨማሪ በሚፈጸምበት ግፍና የቀን ከቀን ህይወቱን ሲኦል ባደረገበት አዋራጅ ድህነት ተማሯል። ይህ ህዝብ እንደ ሰሜን አፍሪካ ህዝቦች የራሱን የፖለቲካ እጣ በጁ ለማድረግ እየተቁነጠነጠ ነው። ነገር ግን ይህ ጥረት በኢትዮጵያ ዉስጥ በሚገኙ ልዩ ሁኔታዎች የተነሳ እንደሌሎች ሃገሮች ቀላል ላይሆን ይችላል። ወያኔ ህብረተሰቡን በዘርና በሃይማኖት እንዲሰነጣጠር እርስ በርሱ እንዲጠራጠር አድርጎታል። የግብጽና የቱኒዚያ ወጣትና ዜጋ እርስ በርሱ ለመነጋገርና መረጃ ለመቀያየርና በጋራ ለማቀድ የተጠቀመባቸው ዘመናዊ በተለይ ከኢንተረኔት ጋር የተያያዙ የኮምኒኬሽን ቴክኖሎጂ ግብአቶች በሃገራችን አልተስፋፉም። ያለውንም ቢሆን የሚጠቀመው ቁጥር አነስተኛ ነው። የመጠቀም እውቀቱም ደካማ ነው። በከተሞች ኗሪ የሆነው ህዝብ አነስተኛነትነው። ከተሞችን ማእከል ያደረገውን የአረብ ሃገሮች ህዝባዊ አመጽ በኢትዮጵያ ለመድገም ይህ ጭብጥ በራሱ ፈተና ነው።

ከዚህ በተጨማሪ የሃገራችን የጦር ሃይል እንደ ሰሜን አፍሪካ ሃገሮች ሃገራዊና ህዝባዊ ተፈጥሮ የለወም። ከዚህም የተነሳ ህዝብ ለነጻነቱና ለመብቱ መከበር ቢነሳ ይህ ጦር እንደግብጽና እንደ ቱኒዝያ ጦር ከህዝብ ጋር ይቆማል ወይንስ ከመለስ ዜናው ጋር ልሙት ይላል? ገና ተጨባች መልስ ያልተገኘለት ጥያቄ ነው። እንደነ ቱኒዝያ ለተወሰነ ጊዜ ችግር መቋቋም የሚችል መሃከለኛ ገቢ ያላቸው በርካታ ዜጎች በሃገራችን የሉም። የሃገራችንን የመገናኛ ብዙሃንም ስርጭት፣ የቴሌቪዥን፣ የሬድዮ የጋዜጣዎች መስፋፋት ህዝባዊ እምቢተኛነቱን በሚያስገርም ክህሎት ካካሄዱት ሃገሮች ጋር ካነጻጸርነው እዚህ ግባ

የሚባል አይደለም። የውጭ ሚድያ ትኩረት፣ ሚድያዎቹ የሚጠቀሙባቸው ቋንቋዎችና ለኢትዮጵያም ሊሰጡ የሚችሉት የሽፋን ጊዜ  አነስተኛነት በህዝባዊ እምቢተኛነቱ ስሉጥነት ላይ የራሳቸውን አሉታዊ ጫናዎች ያሳድራሉ።

ኢትዮጵያን ከነግብጽና ከሌሎች ሃገሮች የሚለይዋት ጭብጦች የሃገራችን ወጣትና ህዝብ በራሱ ሃይል ተንቀሳቅሶ የልቡን እንዳያደርስ ደንቃራዎች እንደሚሆኑበት ግልጽ ነው። እነዚህ ደንቃራዎች በሙሉ ባይጠረጉም የሃገራችን ህዝብ በታሪኩ ከግፍና ከጭቆና ጋር ካደረገው የትግል ታሪኩ ከሚያገኘው የመንፈስ ጥንካሬና የመስዋእትነት ዝግጁነት ተበረታትቶ አሻፈረኝ ብሎ   መነሳቱ አይቀርም። ፈተናዎቹ ከባድና ብዙ ስለሆኑ የሃገራችን ህዝብ፣ በተለይ ወጣቱ በዚህ ወሳኝ ወቅት የሚደረግለትን ማንኛውን ድጋፍ በሙሉ ለመቀበል ዝግጁ ነው።  በዚህ ፈታኝ ወቅት የኢትዮጵያ ህዝብ ከፍተኛ እገዛ ይፈልጋል::   ከሃገር ውስጥ የሚመጡ የወጣቱ ጥያቄዎች ስንመለከት ወጣቱ ተቃዋሚ ድርጅቶች እንዲያደረጉ የሚጠይቋቸው

> *ሁላችሁም ህዝባዊ እምቢተኛነት አመጽ እንዲቀጣጠል እንደምትፈልጉ እናውቃለን። የእኛም የናንተም ፍላጎት አንድ መሆኑን ተረድተናል። እውነተኛ ፍላጎታችሁ ይህ ከሆነ እባካችሁ ዝብርቅርቁ የወጣ፣ እርስ በርሱ የሚጣረስ፣ ትርጉምና መልእክቱ ለወጣቱም ሆነ  ለህዝቡ የማይገባና ውዥንብር የሚያስፋፉ ወረቀት በህብረተሰባችን ውስጥ አትበትኑ። በጋራ መክራችሁ የህዝባዊ እምቢተኛነቱ ትግል የሚያተኩሩባቸውን ጥያቄዎች አሳውቁን።*

የሚሉ ግልጽና ቀላል ነገሮችን ነው።  የተበተኑትን የሚገርሙ ወረቀቶችን ፎቶ እያነሱ ለንቅናቄያችን በኢሜል ልከዋል። እዚህ ላይ መነሳት ያለበት እኛ ተባብረን ባንድ ቃል ካልተናገረን ወያኔ   በእያንዳንዳችን ስም የፈለገውን ወረቀት እያባዛ ቢበትን የሚከለክለው አይኖርም። አንዳንዶቹ በራሪ ወረቀቶች የሚያነሱትን ህዝብ ከህዝብ የሚያጋጭና ህዝብን የሚያስበረግግ ጽሁፍ ለተመለከተ የወያኔ እጅ እንዳለበት ግልጽ ነው።

በግንቦት7 በኩል የምናነበው ሃገራዊ ሁኔታ የሚጠቁመው ህዝብ የዘር፣ የሃይማኖትና ሌሎችንም ከፋፋይ ሊሆኑ የሚችሉ ጉዳዮችን ወደ ጎን አድርጎ ሁሉንም እያዋረደ ባለው የወያኔ አገዛዝ ላይ የድርጅቶችን መሪነት ሳይጠብቅ ለመነሳት እያኮበኮበ መሆኑን ነው። የሃገራችን ወጣቶች “ድርጅቶች መሩን አልመሩን በራሳችን ተደራጅተን ለነጻነታችን የሚከፈለውን መስዋእትነት ከፍለን ነጻ ልንወጣ ቆርጠናል” የሚል መግለጫ እያወጡ ነው። የኦሮሞ ብሄራዊ ወጣቶች እንቅስቃሴ ያወጣው መግለጫ ወጣቱ የየትኛውንም ድርጅት ቡራኬ  እንደማይጠብቅ ገልፆ አድርጓል። ትክክል፣ወጣቶቹ  ፍትሃዊና  የሃገሪቱን ወጣትና ህዝብ በጋራ በወያኔ  ላይ ሊያስነሱ ይችላሉ ያላቸውን ጥያቄዎችን ዘርዝሮ አስቀምጠዋል። የኢትዮጵያ ወጣቶች ንቅናቄ የተባለው ሌላው የወጣቶች ቡድን “የኦሮሞ ወጣቶች ያቀረቧቸው ጥያቄዎች የኔም ናቸው” በማለት ድጋፉን ሰጥቷል። ሌሎችም ወጣቱን በበስፋት የሚያሳትፉ ዘመናዊ የማህበራዊ የመረጃ ድሮች ይህንን የወጣቶቹን ጥያቄ እያስተጋቡ ነው። በኢትዮጵያ ውስጥ ወጣቱ በብዛት በሚገኝባቸው ቦታዎች ወጣቱን ለለውጥ እንዲነሳ የሚጠሩ ወረቀቶች ይበተናሉ። የፖለቲካ ድርጅቶች አገዘነውም አላገዘነውም ወጣቱ ለለውጥ መነሳቱ አይቀርም።

በእንዲህ አይነቱ ሁኔታ የፖለቲካ ድርጅቶች ምን ያድርጉ? ይህ የወጣቶች ሙከራ እንዲሳካ የድርሻችን  ልንወጣ የግድ አይደለም ወይ? ጥያቄው የፖለቲካ ድርጅቶች ከነግዙፍ ድክመቶቻችን ይህን የወጣትና  የህዝብ መነሳሳት የሚያግዙ ስራዎች መስራት አንችልም ወይ?  የዘመኑ ፍቱን የስርአት መቀየሪያ መሳሪያ የሆነውን ህዝባዊ እምቢተኛነትን የመጠቀም ታሪካዊ እድል የሃገራችን ህዝብ እንዳያልፈው የተለያዩ  የፖለቲካ ድርጅቶች በጋራና በፍጥነት ተመካክረው አንድ ነገር ማድረግ አይኖርባቸውም ወይ? እነዚህ ጥያቄዎች ፈጣን ምላሽ የሚጠይቁ መሆናቸው ነው፣ በድርጅቶች መሃል የመመካከርና የመተባበርን ጉዳይ አስቸኳይ ያደረገው።

## 3. ማነው አደገኛ - ህዝብ ወይስ የፖለቲካ ድርጅቶች?

የፖለቲካ ድርጅቶች በመካከላቸው ያሉትን እውን ወይም እውን ያልሆኑ ልዩነቶቻቸውን አስወግደው መሰባሰብና መጠናከር እስከሚችሉ ድረስ ወጣቱ እጁን አጣጥፎ ይጠብቅ ከተባለ ለዘላለሙ በባርነትና በድህነት እንዲኖር እንደመፍረድ የማይቆጠረበት ምንም ምክንያት አይኖርም።

ሰሞኑን የወያኔ ተቃዋሚ ነን ከሚሉ ግለሰቦችና ቡድኖች “ጥንቃቄ እናድርግ” በሚል ምክንያት የሚቀረቡ ጽሁፎች በአለማችን በተለይ በአፍሪካና በመካከለኛው ምስራቅ ዉስጥ በፍጥነት እየተቀየረ ያለውን ሁኔታ ያገናዘቡ አይመስሉም። “የኢትዮጵያ ህዝብ በወያኔ ላይ ቢያምጽ አገሪቱ ታላቅ ቀውስ ላይ ትወድቃለች። የሃገሪቱ ጠላቶች የሆኑ የውጭ ሃይሎች አጀንዳቸውን ለማስፈጸም ቀውሱን ሊጠቀሙበት ይችላሉ። የመገንጠል አላማ ይዘው የተቀመጡ ሃይሎች የወያኔ መንግስት በህዝባዊ እምቢተኛነት ቢናጋ የመገንጠል አላማቸውን ለማሳከት እድል ያገኛሉ” እያሉ ነው። መፍትሄ ብለው የሚያቀረቡት ሃሳብ የድርጅቶች ትብብርና ህብረት በቅድሚያ እንዲኖር ማድረግ እንጂ ይህን ወጣት ለመደገፍ ምክክር አያስፈልግም የሚል ነው። ህዝቡ በተለያዩ ሃገሮች  ያለፖለቲካ ድርጅቶች መሪነት በራሱ እንዲያምጽ ያደረገው ይህን ትብብር ተቃዋሚ ድርጅቶች ለአመታት ማምጣት የተሳናቸውና ፖለቲካዊ  ሃላፊነታቸውን መወጣት አለማቻለቸው እንደሆነ እነዚህ ሃይሎች የተረዱት አይመስልም። ለመሆኑ  በሁሉ ጉዳዮች ላይ ያለቀለት ካልሆነ በስተቀር በመለስተኛ የጋራ አላማዎች ዙሪያ መተባበር አይቻልም ወይ?  ለመሆኑ “እኛ ዝግጁ አይደለንምና የህዝባዊ እምቢተኛነቱ ቁጣ ቢቀሰቀስ በሃገሪቱ ውስጥ ቀውስ ይፈጠራል።  መጀመሪያ እኛ ዝግጁ እስክንሆን የመለስን መንግስት አትነካኩት” የሚል መልእክት የኢትዮጵያ ተቃዋሚዎች ለማስተላለፍ ምን የሞራልና የስራ ሬኮርድ አለን? የኢትዮጵያ ህዝብ እንደ ቱኒዝያና ግብጽ ህዝብ ተነስቶ “መብቴ  ይከበር” ቢል ከዚህ የመብት የማስከበር ፍላጎት ውጭ ተንቀሳቅሶ አገር የሚጎዳበትሁኔታ ሊኖር ይችላል የሚል ስጋት ሊኖረን ይገባል ወይ? በጋራ የግፍና የሰቆቃ የድህነትና የውርደት ህይወት ተሳስሮ፣ ከዳር እስከ ዳር ባንድነት በመለስ ዜናዊ ላይ የሚነሳው ህዝብ ነው ወይንስ የራሳቸው ጠባብ የድርጅት አጀንዳዎችና የስልጣን ፍላጎቶች ያሏቸው ድርጅቶች ናቸው ለኢትዮጵያ ህዝብ የሰላም፣ የዴሞክራሲና አንድነት አደጋ የሚሆኑት? ያለፉት 20 አመታት ከተፈለገም ከዛ በላይ የሚዘከርለት የኢትዮጵያ ተቃዋሚዎች የነጻ አውጭነት ታሪክ ምን ያህል አስተማማኝ  ነው?  “የተደራጀ አምባገነን በአንድነት ተባብረን እንደ አንድ ሰው ሆነን ካልገጠምነው ለዘላለም ባሪያ አድርጎ  ሊገዛን ነውና በአንድነት እንነሳ” በሚል የጋራ ግንዛቤ ከፖለቲካ ድርጅቶች ጀርባ መነጋገር የጀመረ ህዝብ መለስን በማስወገድ ወይም በማንገዳገድ የአንድነትን ሃያልነት በሚረዳበት ወቅት እንዴት ሆኖ አንድነቱን የሚያናጉና የሌላ አምባገነንና ዘራፊ ቡድን ሲሳይ ሊያደረጉት ወደሚችሉ ራስን የማውደም ተግባር የሚመለሰው? የቅርብ ጊዜ አብዮቶች ይህን አይነት የህዝብ አላዋቂነት የጠቆሙበት ማስረጃ  አለ ወይ? በደንብ ከተመለከትነው ማስረጃው ከዚህ የተለየ ነው። በየሃገሩ የተገረሰሱ አምባገነኖች በየሃገሩ እንደነበሩ ደካማ ተቃዋሚዎች ቢሆን ኖሮ በድርድርና በስምምነት በስልጣናቸው ላይ በቀጠሉ ነበር። ለፈጸሙትም ወንጀል ተጠያቂ ባልሆኑ ነበር። ህዝብ ባንድነትና በጽናት ቆሞ “ድርድር የለም፤ መንፏቀቅ የለም። በቃ!” ባይላቸው እንሙባረክ ለልጆቻቸው ስልጣናቸውን ለማውረስ ተቃዋሚው የሚጋርጥባቸውን ፈተና ለማለፍ የሚያስቸግራቸው አይሆንም ነበር።

በሃገራችን ያሉ የፖለቲካ ድርጅቶች ምን አይነት ድርጅቶች እንደሆኑ፤ በምን ያህል ትጋትና እልህ እንዲሁም የሁኔታዎችን አሳሳቢነት ግምት ውስጥ እያስገቡ በጥድፊያ እንደሚሰሩ፤ ምን ያህል አባላትና ድርጅታዊ መዋቅር እንዳላቸው፣ በማስፈራሪያና በድለላ የያዙትን አቋም በቀላሉ ሊቀይሩ እንደሚችሉ ብዙ ከህዝብ የተሰወረ ጉዳይ አይደለም።  ህዝብ ያለው ትልቅ ተስፋ የራሱን የነጻነት ትግል ራሱን አታጋይና ታጋይ አድርጎ  የሚከፈለውን መስዋእትነት ከፍሎ ማረጋገጥ ብቻ ነው። የቱኒዝያና የግብጽ ህዝብ ለማድረግ የሞከረው ይህንኑ ነው። ግብጾችን ቱኒዝያኖች ከኢትዮጵያውያን የተለዩ  ፍጥረቶች ናቸው ካላልን በስተቀር የሃገራችን ወጣቶች “ለነጻነታችን ልንነሳ ነው” ሲሉ “ተው ጠብቁን” የምንልበት ምክንያት ሊኖር አይችልም፤ አይገባምም። እንዲያውም ያለንበትን ሁኔታ  በደንብ ከተመለከትነው ጠንካራ ድርጅቶች ወይም ድርጅት በሌለበት ሁኔታ የአንድ ሃገር ህዝብ በስፋት ተነስቶ  የራሱን የወደፊት እጣ በጁ ማስገባት የሚችለበት እድል መገኘት አምባገነንትን ከአንድ ሃገር ላይ ለአንዴና ለመጨረሻው መቅበሪያ ፍቱን  መሳሪያ  ነው። በጠንካራ ድርጅቶች ከሚመራ የዴሞክራሲ የለውጥ እንቅስቃሴ ይልቅ ለራሳቸው ህይወት ሃላፊነት በወሰዱ በሚሊዮኖች የሚቆጠሩ ዜጎችና በሽዎች የሚቆጠሩ የዜጎች ቡድኖች የሚመራ ትግል ለዴሞክራሲ ግንባታ ተመራጭና አስተማማኝ ነው። የህዝብ አቅም ሳይደረጅ የድርጅቶች አቅም ከሚገባው በላይ ማደግ ለህዝብ አደጋ ያረገዘ አካሄድ ነው። ህዝብ በሚነሳበት ወቅት መስዋእትነቱ መና እንዳይቀር መደረግ ያለበትን ዝግጅትና ጥንቃቄ እንዲደረግ የራሳችን ሃላፊነት እስከተወጣን ድረስና የህዝብም ትግል በድል እስከተጠናቀቀ ድረስ የድርጅቶች ትብብር ጠንካራ ሆነ አልሆነ ከዲሞክራሲ ግንባታ አንጻር ካየነው የሚሳሳብ ጉዳይ አይደለም።

ድርጅቶችና መሪዎች የዴሞክራሲና የነጻነት ቃል ኪዳናቸው ሊሰብሩ የህዝብ አደራ ሊበሉ ይችላሉ። ህዝብ ግን ራሱን በራሱ የሚጎዳ ስራ ስለማይሰራ ለገዛ ነጻነቱና መብቱ ዘላለም ዘብ ይቆማል። በኢትዮጵያም የሃገሪቱ ተቃዋሚ ድርጅቶች ደካማ በሆኑበት ሁኔታ ህዝብ የተሳካ የህዝባዊ እምቢተኛነት ቁጣ ማቀጣጠል ከቻለ ለህዝብና ለሃገር የሚጠቅም እንጂ የሚጎዳ አይደለም። የህዝብ ጉልበት ከድርጅቶች ጉልበት በላይ የሚያይለበት ሁኔታ በሃገራችን ቢከሰት በየጊዜው ስልጣን ለሚይዙ አምባገነን ባለጌዎች መቀለጃ ሆኖ ስቃዩ ማብቂያ ላጣው የሃገራችን ህዝብ እንደጸጋ መታየት ይኖርበታል። ስለዚህ ህዝብ "ለመብቴ እነሳለሁ!" ሲል መልሳችን "እንዴት በጥድፊያ እናግዘው?" ነው እንጂ ይህን እገዛ የሚያጓትቱና በአንድነት መቆም የሚገባቸውን ድርጅቶችንና ቡድኖችን በማይረባ እንቶ ፈንቶ የሚጠመዱ አጀንዳዎችን መክፈት፣ ማስፈራሪያዎችን ማሰራጨት የወቅቱ ተገቢ ምላሽ አይሆንም።

## 4. አዲሱ ዘመን - አዲስ አይነት ትብብር

ባሁን ወቅት የሚስተጋባው የትብብር ጥሪ "ግንባር እናቁም፤ ትብብር እንፍጠር፤ መድረክ እናዘጋጅ፤ ወያኔን ለመተካት የሚችል የቀውጢ ጊዜ ግብረ ሃይል ወይም ተተኪ መሆን የሚችል የመንግስት ቅጂ (ጥላ) እናቁም" አይደለም። "የተለያዩ የድርጅት ፕሮግራሞችና ፖሊሲዎቻችን እናቀራርብ" የሚልም አይደለም። ደግመን ደጋግመን እንለዋለን ድርጅቶች ጠንካራ ህብረቶችን ፈጥረው መገኘታቸው አስፈላጊም ጠቃሚም ነው። ቀደም ብለን እንደጠቀስነው የተቃዋሚዎች አቅም በአንድ ተደምሮም ዝቅተኛ በመሆኑ ህዝብን የሚያስፈራ አይሆንም። ከአቅማቸው ማነስ የተነሳ ተቃዋሚዎች ባንድ ላይ ተሰብስበውም ባሁኑ ወቅት ህዝብን ከማበረታት አልፈው የመሪነት ሚና መጫወት አይችሉም። ለትብብር መፍጠር የሚደረገው ሙከራ አሁንም ይቀጥል። ነገር ግን አዲሱ ዘመን ይዞት የመጣውን አዲስ የትብብር እይታም በደንብ እንፈትሸው።

የግብጽና የቱኒዝያ አብዮቶች ያስተማሩን ትምህርት ህዝብ የሚቆጣጠረው የለውጥ ሂደት በፖለቲካ ፓርቲዎች መሃከል ያለውን ማናቸውንም ልዩነት ወደ ዝቅተኛ ደረጃ ማውረድ እንደሚችል ነው። ቅድሚያ ሁሉንም የሃገሪቱ ዜጎችና የፖለቲካ ድርጅቶች በእኩልነት የሚያስተናግድ ዴሞክራሲያዊ ሁኔታ ለመፍጠር ለሚደረገው ትግል መስጠት እንደሚቻል ነው። የቱኒዝያና የግብጽ ህዝባዊ እምቢተኛነት የፖለቲካ ድርጅቶችን የለውጥ መሪነት ወይም ተቆጣጣሪነት ሚና በመዘጋትና በብዙሃን ቡድኖች አማካይነት በህዝብ ለሚከወን አብዮት እድል በመክፈት የትግሉን ህዝባዊ አንድነትንና የተነሳበትን አላማ መከላከል ችሏል።

ከህዝብ ጀርባ በልሂቁ መሃከል በሚደረግ የሰጥቶ መቀበል ድርድር ስልጣን ለመያዝ የሚደረግ ትብብር የዘመኑ የትብብር ጥያቄ አይደለም። ህዝብም እንዲህ አይነቱን አግላይ የፖለቲካ አካሄደ እሺ ብሎ የሚቀበልበት ዘመን አልፏል። ያለንበት ዘመን የፖለቲካ ድርጅቶች መተባበር ጽንጸ- ሃሳብ ቀላልና ኩልል ብሎ የሚታይ ነው። ተሰባስበን ተመካክረን ተባብረን ህዝብ በራሱ መሪነት ሊያከናውነው የሚፈልገውን የነጻነት ትግል እንዴት እንደግፍ በሚል ጉዳይ ላይ ያተኮረ ነው፤ የዘመኑ የትብብር ጥሪ። የተወሳሰበ ድርጅታዊ መዋቅር፣ ሰነድ፣ የግንባር የስልጣን ክፍፍል ወዘተ የመሳሰሉ አጨቃጫ ጉዳዮች የሉትም ። መሃመድ ቦዓዚዝ ራሱን አቃጥሎ የቱኒዝያ ህዝብ በቁጣ እንዲገነፍል ካደረገበት እለት ጀምሮ ግንቦት 7 ከየትኛውም ድርጅትና ቡድን ጋር ያደረገው የትብብርና የምክክር ስራ የዘመናችን የለውጥ እንቅስቃሴ ግምት ውስጥ ያስገባ ነው።

ህዝብ በግብጽ እንደታየው በአንድነት ለነጻነቱና ለዴሞክራሲያዊ ስርአት መመስረት እንዲነሳ ራሱን ብቻ ሳይሆን በተለያዩ ምክንያቶች ተሸመድምደን የምንገኘን የፖለቲካ ድርጅቶችን ነጻ እንዲያወጣ ምን ማበርከት እንችላለን? ህዝብ ማንም ሳይጠበቅ የሚነሳ ከሆነ ጥረቱ እንዲሳካ ለህዝብ ምን ድጋፍ ልናደረግ እንችላለን? ይህ ነው ያለፉት ጥቂት ወራት የግንቦት7 ንቅናቄን ትኩረት የሳበው። ባለፉት ጥቂት ወራት ግንቦት7 ግንባር፣ ቅንጅት ወይም ውህደት እንፍጠር በማለት ያነጋገረው ድርጅት የለም። የፈጠረውም ግንባር የለም። ትልቁንና ብዙ ጣጣዎች ያሉትንና ብዙዎች ብዙ ጊዜ ሞክረውት ያልተሳካ ከባድ የግንባር፣ የቅንጅትና የውህደት መፍጠር ስራ ግዜውን ጠብቆ በሂደት ሊከናወን እንደሚችል እምነት አለን። ይህ ሂደት አዝጋሚ ነውና ፈተናዎቹ ብዙ ናቸውና እንተወው አላልንም። ሆኖም ግን ባለፉት ጥቂት ወራት ንቅናቄያችን ያተኮረው እጅግ አጣዳፊ በሆኑና በቀላሉ በመመካከር ሊፈጸሙ በሚችሉ የጋራ ጉዳዮች ላይ ነው። ለነጻነቱ የሚነሳውን ህዝብ በጋራ

የመታደግ ስራ ላይ ነው። "ለህዝብ ሙብት መከበር ቆሚያለሁ" ከሚል ማናቸውም ሃይል የሃገራችን ወጣትና ህዝብ በአሁኑ ወቅት የሚጠብቀው ይህን ብቻ እንደሆነ እርግጠኞች ነን።

ሁላችንም በፖለቲካው መድረክ የምንቀሳቀስ ድርጅቶች ቡድኖችና ግለሰቦች ልብ ልንለው የሚገባ ሌላ ሃቅ አለ። ዛሬ ሁላችንም የኔ እያልን የምንጠራቸው፤ በየትኛውም ኪሳራ ህልውናቸውን ልንከባከብላቸው የምንጥራቸው ድርጅቶቻችን ወደፊት በሃገራችን ውስጥ በሚቀሰቀሰው ሰፊ ህዝባዊ የነጻነት ማእበል ወስጥ እጣቸው ምን እንሚሆን ለመተንበይ አስቸጋሪ መሆኑን ነው። ስለትብብር፣ ስለ ሽግግር መንግስታዊ ስርአት መመስረት ስናወራ ሁኔታዎች እንዳሉ ይቀጥላሉ የሚል እሳቤ እያስቀመጥን ነው። በሚሊዮኖች የሚቆጠሩ ዜጎች ለሙብታቸው በሚንቀሳቀሱበት ሁኔታ ታፍኖ ከኖረው ህዝብ መሃል አዲስና ግዙፍ ድርጅቶች ሊወለዱ፣ የህዝብን አመኔታ የሚያገኙ ታላላቅ መሪዎች ብቅ ሊሉ ይችላሉ። ዛሬ ያለነውን ድርጅቶች ላይ በማተኮር "የሃገሪቱ ፖለቲካ አልፋና ኦሜጋ እኛ ብቻ ነን" የሚል መንፈስ ሁሉን አድቀን ወስነን ጨርሰን እንሂድ የሚል የትብብር አመለካከት ይህንንም እውነታ ግምት ውስጥ ማስገባት ይኖርበታል።

ከህዝባዊ እምቢተኛነት የፈለቀው አዲሱ የትብብር ቀመር ለድርጅቶች ብትህውትነት ያስተማረ ይመስለናል። "ያለኔ የህዝብ ተጠሪ የለም። ያለኔ ዲሞክራሲ አይኖርም።ያለኔ ሃገር ይፈረሳል። ህዝብ እርስ በርሱ ይጫረሳል" የሚለውን የየሃገሩን ልሂቅ ትምክህት አስተንፍሷል።

## 5. ያለ ህዝባዊ አንድነት ነጻነት እንደማይኖር የገባው ወጣትና ህዝብ

የሃገራችንም ህዝብ ወያኔን ለማቸነፍ የግድ የትግል አንድነት መፍጠር እንዳለበት ያውቃል። ወያኔን በማሸነፍ የሚቀዳጀውን ድል ለመከላከል አንድነቱን ጠብቆ መሄድ እንደሚገባው የሚስተው አይደለም። የቱኒዝያን የግብጽ ተመክሮ የሚያሳየው ይህንኑ ነው። አሁንም ኢትዮጵያውያን እንደ ግብጾች አርቆ አሳቢ አይደሉም ካላልን በስተቀር። ይህ እውቀት ደግሞ ጠባብ የሆነ የድርጅት አጀንዳዎች የሚያስተናግድበት ሰፊ ሆድ አይኖረውም። የህዝብ የመታገያ ጥያቄዎች ሁሉንም ህዝብ በጋራ ማንቀሳቀስ የሚያስችሉ እንጂ አንዱን ወገን ተቀብሏቸው ሌላው ወገን የኔ አይደሉም የሚላቸው ሊሆኑ አይገባም። አድማሳዊ የሆኑ የሙብት፣ የነጻነት፣ የፍትህና የእኩልነት ጥያቄዎች ብቻ ናቸው የሃገሪቱን ህዝብ በአንድነት እንዲጓዝ የሚያደርጉት። ከዚህ ውጭ ሁሉም በየራሱ አጀንዳ እንመራ ካለ የቱንዚያና የግብጽ ህዝብ በአምባገነን መሪዎቹ ላይ የተቀዳጀውን ድል የኢትዮጵያ ህዝብ መቀዳጀት እንደማይችል ያውቃል።

በጣህሪር አደባባይ ቁራንና መስቀልና የያዙ አማኞች ያስተላለፉት መልእክት "ሙባረክንና ጓደኞቹን ማሸነፊያ መሳሪያችን አንድነታችን" ነው የሚል ነበር። ይህ መልእክትና ትርጉሙ በአለም ላይ ከጭቆና ለመውጣት ለሚታገሉ ህዝቦች ደርሷል። ከዚህ መልእክት በፊትም ይህንን ሃቅ ተራ በተራ በወያኔ እየተቀጠቀጠ ያለው ዜጋ በሙሉ ያውቀዋል። የሃገሪቱ ህዝብ ከሌሎች ሃገሮች ልምድ የቀሰመውን ወሳኝ ትምህርትና ራሱም በደመነፍሱ የሚሰማው ስሜት የትግል አንድነት መፍጠር በአምባገኖች ላይ የማያዳግም ድል ለመቀዳጀት ወሳኝ መሳሪያ እንደሆነ ነው።

በኢትዮጵያ ያለው የእምነት ልዩነት ብቻ አይደለም። ኢትዮጵያ በርካታ የተለያዩ የዘውግ ማህበረሰባት ያሉባት ሃገር ናት። ወያኔ ደግሞ የተለያዩ ዘውጌ ማህበረሰባትን እርስ በርሳቸው እንዲናከሱ ለማድረግ ያልጠነሰሰውና ያልተገበረው ሴራ የለም። ወያኔን እንቃወማለን የሚሉ ድርጅቶችም በቀጥታ በሰሯቸውና ባልሰሯቸው ስራዎቻቸው ይህን የወያኔን ከፋፍሎ የመግዛት እኩይ ስራና ከዚህ የመከፋፈል ሴራው ያገኘውን የተጋነነ አቅም ማርከስ ሳይችሉ እስካሁን ቆይተዋል።

አሁን ግን ህዝብ ራሱ መከፋፈሉ የባርነት ሰንሰለቱን ማጥበቂያ እና በጥቂቶች የመረገጫና የመዘረፊያ ምክንያት መሆኑን ተረድቷል። "ተለያይተን በማመጽ ወያኔ በተናጠል እንዲመታን እድል አንስጠው። በሁሉም የሃገርቱ ክልል በአንድ ግዜ በአንድ ላይ ተነስተን ወያኔ ምንም ሊያደርገን እንደማይችል እናሳየው። የሁላችንም ስብእና የሚያከብር ለሁላችንም በእኩልነት የሚያይ ሙብታችን የሚንከባከብ የስርአት ለውጥ እናምጣ" ነው ህዝብ የሚለው። ማህበረሰቦች እንዳይገናኙና ወያኔ የዘረጋውን ዘረኛ የጥቂቶች ስልጣን እንዳይፈታተኑ በማሰብ አገዛዙ ሰብሮት የነበረው ድልድይ ወያኔ በሁሉም ማህበረሰብና ዜጋ ላይ በሚያዘንበው የግፍና የውርደት ጎርፍ የተነሳ ተመልሶ እንዲገነባ የግድ ሆኗል። የዛሬን ፈተና አልፎ ነገ ለልጆቹ የተስፋ ሃገር ማውረስ የሚቻለው ስቃይና ግፍ በቃ ብሎ በአንድነት መነሳት እስከቻለ ድረስ እንደሆነ የሃገሪቱ

ህዝብ ከተረዳ ሰንብቷል። የቱኒዝያና የግብጽ አብዮት ያደረገው ነገር ቢኖር ይህ የሃገራችን ህዝብ ግንዛቤ ትክክል እንደሆነ ተጨማሪ ማስረጃ መስጠት ብቻ ነው።

ይህ አንድነት የቆመው የጋራ ሰብአዊ ክብርን ለመቀዳጀት፤ በጋራ ነጻነትን ለመጎናጸፍ፤ በጋራ ከዘረፋና ከድህነት ለመገላገል ነው። የኢትዮጵያ ህዝብ የሃገሩ ግዛታዊ ወይም ሉአላዊ አንድነት በህዝብ ቁጥጥር ስር የሚውል መንግስት ሳይኖር መረጋገጥ የማይችል እንደሆነ በሚገባ የተረዳ ህዝብ ነው። የኢትዮጵያ ህዝብ አምባገነናዊ በሆነ መንገደ የግዛት አንድነትን እናስከብራለን በሚል መንገድ ለተጓዙ አገዛዞች ብርቅየ ልጆቹን ገብሮ የተማረው ትምህርት አምባገነናዊ ስርአቶች አንድነት እንደማያስጠብቁ ነው። ልኡላዊ የግዛት አንድነት ሆነ ማህበረሰባዊ አንድነት ከዴሞክራሲ ስርአት ምስረታ ውጭ ሊከበር እንደማይቻል የሚያውቅ ህዝብ ቅድሚያ በዜጎች አንድነት ላይ ለቆመና ለዴሞክራሲ የሚደረግ ትግል መስጠቱ ትክክልና ተገቢ ነው።

ግልጽ የሆነ የአንድነትና የዴሞክራሲን ችግሮች ሊፈታ የሚችል የትግል ሂደት በሃገር ወስጥና ከሃገር ወጭ መልክ እያያዘ እየመጣ ነው። በፖለቲካ ድርጅቶች መሪዎች አካባቢ ካለው በጋራ የመስራት ፍላጎት በላቀ ደረጃ የተለያዩ ብሄርና ብሄረሰብ አባላትና ማህበረሰባቸው በአንድነት ለመስራት በስሜት የሚንቀሳቀሱት የማህበረሰቦችና የዜጎች አንድነት የነጻነት ምንጭ መሆኑን በሚገባ በመረዳታቸው ነው። የኦሮሚያ ወጣቶች የሃገሪቱን ህዝብ በሙሉ ስቃይና በደል የሚገልጹ ጥያቄዎች አንስተው በጋራ እንታገል የሚል ጥሪ ሲያቀረቡ ይህንኑ አንድነት፣ ለነጻነታችንንና መብታችን መከበር መሳኝ ነው የሚል መልእክታቸውን እያስተጋቡ ነው። የአትላንታ፣ የኦጋዴንና የኦሮሞ ማህበረሰብ ተወካዮች ከግንቦት 7 አመራር ጋር ህዝባዊ ስብሰባ አድርገው ለመብታችን መከበር፣ ግፍና ሰቆቃ እንዲያበቃ ትከሻ ለትከሻ ተደጋግፈን እንቁም ሲሉ ያስተጋቡት መልእክት በመላው ሃገሪቱ ውስጥ በመለስ ዜናዊ ዘረኛ አገዛዝ ግፍና መከራው የመረረውን ዜጋ ሁሉ ስሜት የሚያንጸባርቅ ነው። በሌላ በኩል ደግሞ እንዲህ አይነቱን ከጋራ ስቃይ የመጣ የማህበረሰባችንን የመቀራረብ ጥሪ አንደኛው ድርጅት ሌላውን አዘናግቶ ለመመታት የሚደረግ የሴራ ውጤት እንደሆነ አድርገው የሚያቀረቡ ድርጅቶችና ግለሰቦች እያየን ነው። እንደ ግንቦት7 አመለካከት እነዚህ አካላት እንዲህ አይነቱን አቋም መያዝ የቻሉት በአፍሪካችን እየነፈሰ ያለው ነፋስ ህዝብ ባንድ ላይ በግፍ አምራቾች ላይ እንዲነሳ እንጂ የድርጅቶች ሴራ መሳሪያ የሚሆነበትን ሁኔታ የማይጠቁም እንደሆነ ካለማጤን የመጣ ነው ብሎ ያምናል። ይህንን በደንብ ሳያጤኑ፣ በአለንበት ዘመን ከዲሞክራሲ ስርአት ውጭ የሃገር አንድነት ይከበር ይመስል የፖለቲካ ቡድኖችንና ማህበረሰቦችን ከፊሎቹን "የአንድነት ሃይሎች" ከፊሎቹን ደግሞ "የጸረ አንድነት ሃይሎች" በሚል ፍረጃ በሃገራችን ለዴሞክራሲ በአንድነት የሚደረገውን ትግል መከፋፈል ማንን እንደሚጠቅም ለማወቅ ብዙ ምርምር አይጠይቅም።

የችግሮች አደራደርና አቀማመጥ በመፍትሄያቸው አሰጣጥ ላይም የራሱ የሆነ ተጽእኖ እንዳለው መረዳት ተገቢ ነው። ዛሬ በኢትዮጵያ ያሉትን ችግሮች በሙሉ ብንደረድራቸው መፍትሄያቸው ከዴሞክራሲ አለመኖር ጋር በቀጥታ ይተሳሰራል። ወያኔ በያዘው መንገድ እንዲነጉድ እድል ከተሰጠው ኢትዮጵያ እንደ ሃገር ህልውናዋ የመቀጠሉ ጉዳይ አጠራጣሪ ነው። ይህ ግንቦት 7ን በእጅጉ ያሳስበዋል።

ግንቦት 7 ስለአንድነት ብዙ ስለጻፍን፣ ስላወራን፣ ስለዘመርን፣ ስላቅራራን በሃገራችን ላይ ያንዣበበውን የመበታተን አደጋ እናስወግደዋለን ብሎ አያምንም። የሃገራችንን አገራዊ ጥቅምና አገራዊ ደህንነት የሚጎዱ ማለቂያ የሌላቸው ድርጊቶች በወያኔ ሲፈጸሙ ቆይተዋል፤ እየተፈጸሙም ነው። ወያኔ ተወግዶ ሌላ ሃይል ስልጣን ላይ ቢመጣ እንኳን ለሃገራችን ህልውና ዋስትና የሚሰጠን የህዝብ የበላይነት የሰፈነበትን ዴሞክራሲያዊ ስርአት መገንባት ስንችል ነው።

ኢትዮጵያ ረሃብ፣ በሽታ፣ መሃይምነት፣ ዘረፋ፣ አፈና ሰቆቃ የተንሰራፋባት ሃገር ናት። የእነዚህ ችግሮች መፍትሄ ዞሮ ዞሮ ህዝብን የሚፈራና ስራው በህዝብ የሚፈተሽ፣ ለህዝብ ተጠያቂ ከሚሆን መንግስታዊ አስተዳደር ምስረታ ጋር ይያዛል። ዲሞክራሲ ከመሰረታዊ ችግሮቻችን ጋር ያለው ትስስር ፍንትው ብሎ የሚታይ ጉዳይ ነው። "በፖለቲካ ድርጅቶች መሃል የሚደረግ የወቅቱ ምክክርና ትብብር ቅድሚያ ለዲሞክራሲ በሚሰጡ ሃይሎች እንጂ ሌላ ነገር ለሚያስቀምጡ ሲሆን አይገባውም" የምንለው ለዚህ ነው። "የኢትዮጵያ ችግር የአንድነት ችግር ነው ወይስ የዴሞክራሲ?" የሚል ጥያቄ ቢቀርብ "ችግራችን የአንድነት ችግር" የሚሉ ብዙዎች ይኖራሉ። ሆኖም በጥሞና ከታሰበ የሃገራችን ችግር የዲሞክራሲ አለመኖር

መሆኑን፤ የአንድነት ችግራችን በዲሞክራሲያዊ ስእአት መመስረት በቀላሉ የሚቃለል መሆኑን መረዳት የሚቸግረን አይመስለንም።

ሃሳቦችን ችግር በመፍቻነት በማቅረብ እና ሃሳቦችን ለፕሮፓጋንዳ መሳሪያነት በመጠቀም መሃል ትልቅ ልዩነት አለው። የሃገር አንድነት ጉዳይ የሚያሳስበው በርካታ ዜጋ አለ በሚል ስሌት የኢትዮጵያን ችግር በአንድነትና በጸረ አንድነት ሃይሎች መሃከል በሚደረግ ትግል እንደሚፈታ አድርጎ ማቅረብ ሃቀኛነት የጎደለው አካሄድ ነው የምንለው ለዚህ ነው። የኢትዮጵያ ችግር ለአንድነት በቆሙና የመገንጠል አላማ ባላቸው ድርጅቶች መሃከል ብቻ የሚያጠነጥን አይደለም። ለዴሞክራሲ በቆሙ የአንድነት ሃይሎችና ለዴሞክራሲ ባልቆሙ የአንድነት ሃይሎች መሃከል ያለው ችግርም በቀላሉ መታየት የለበትም። ጠባብ የቡድን ፍላጎት ለማራመድ ሲል ለዜጎችና ለማህበረሰቦች ነጻነት የሚከለክል የአንድነት ቡድን ለጠባብ ፍላጎትና ጥቅም ሲል የመገንጠል አላማ የሚያራግብ ቡድን ከሚፈጥረው ችግር ያልተናነሰ ችግር ሊፈጥር ይችላል።፣

በተለይ ባሁኑ ሰአት የሀገራችን ህዝብ በሙሉ በጸረ አምባገነንት ትግል ዙሪያ ለመቆም ዝግጅት እያደረገ ነው። ባለፉት ሃያ አመታት አንዱ ማህበረሰብ ሌላውን እንዲጠራጠርና እንዲፈራ ያደረጉ በርካታ የጭካኔ ተግባራትና የጥላቻ ፕሮፓጋንዳ ስራዎች ተሰርተዋል። የህዝባዊ አንድነት ጉዳይ ገና መሄድ እንደጀመረ ህጻን ወፌ ቆመች እየተባለ የሚበረታታ እንጂ አንዳንድ ጸረ_ወያኔ ነን የሚሉ ቡድኖች እንደሚያደረጉት የጥቃትና የዘለፋ ኢላማ ሊሆን አይገባውም። ወያኔ በኢትዮጵያ አንድነት ላይ ከፈጠረው አደጋ በላይ በአካባባዊና በሀገራዊ ሁኔታዎች እየተገፉ በጋራ ለመስራት ጥረት የሚያደርጉ የማህበረባችን አባላት በምን ስሌት ነው የሃገራችን አንድነት የከፋ አደጋ ተደርገው የሚታዩት። ወያኔን የሚያህል ጸረ-አንድነት ሃይል አስቀምጦ፣ በአንድነት ለመስራት እጆቻቸውን እየዘረጉ ያሉ የማህበረሳባችንን አባላት አታስጠጉ የሚል መልእክት መነሻው ምንድነው? ችግር ለመፍታት የሚደረግ ነፍስ ቡርቦራና ርካሽ የፕሮፓጋንዳ ቀቢጸዊ እርካታ ለማግኘት የሚሰሩ ስራዎች ትልቅ ልዩነት አላቸው። የፕሮፓጋንዳ አዋራ ከረገፈ በኋላ የሚቀረው ያው እፍ ብንል የማይጠፋው እውነታ ነው። ያ እውነታ የኢትዮጵያ ችግር በዴሞክራሲያዊ ሃይሎችና በጸረ_ዴሞክራሲ ሃይሎች መካከል በሚደረግ ትግል ብቻ የሚፈታ መሆኑ ነው። <u>የአንድነቱም አደጋ ምላሽ የሚያገኘው በዚሁ በዲሞክራሲ ማእቀፍ ውስጥ ብቻ ነው።</u>

ያለዜጎች አንድነት በኢትዮጵያ ውስጥ የሚደረገው ጸረ -አምባገነናዊ ትግል የትም እንደማይደረስ ለሁሉም ዜጎች ግልጽ በሆነበት ባሁኑ ወቅት የተለያዩ ፕሮግራሞች ያሏቸው ድርጅቶች ሊያነሱ የሚገባው ጥያቄ እንዴት አድርገው ይህን የህዝብ የትግል አንድነትና ስሜት ማበረታት ይችላሉ የሚል ነው። የወቅቱ በድርጅቶች መሃከል የሚደረግ ውይይት እንዲህ አይነቱን ጉዳይ በዋንኛት መነጋገሪያው ሊያደረገው ይገባል የሚል እምነት አለን።

## 6. ለአጋርነት እንጂ ለመሪነት ያልበቃ ተቃዋሚ

የፖለቲካ ድርጅቶች አንድ ህዝብ ከደረሰበት ንቃተ ህሊና ላይ የተመረኮዘ እቅድ ያወጣሉ እንጂ እነሱ ባንድ ወቅት ይዘውትና ለመልቀቅ ወደማይፈልጉት አመለካከትና ተግባር ህዝብን መጎተት የለባቸውም። ዘመኑ ህዝብ ራሱን በራሱ አደራጅቶ የራሱ ነጻ አውጭ መሆን የሚችለባቸውን አዲስ የነጻነት የትግል ሂደት የተከፈተበት ዘመን መሆኑን ሁላችንም መረዳት አለብን። “አንድ የተማከለ የፖለቲካ ድርጅት ወይም የተወሰኑ የፖለቲካ ድርጅቶች ግንባር ፈጥረው የለውጥ ወኪሎች ካልሆኑ በአንድ ሃገር ላይ ለውጥ መምጣት አይቻልም” የሚለው ነባር አመለካከት ከፉኛ የተመታበት ዘመን ላይ ደርሰናል። በፖለቲካ ልሂቁና በህዝብ መካከል የነበረው ግንኙነት በሞግዚትና በህጻን መሃከል እንደሆነ ተደርጎ ሲሰራበትና ለተከታታይ አምባገነናዊ ስርአቶች መመስረት ምክንያት የነበረው እንከን የተነቀለበት የታሪክ ምእራፍ ላይ ነን። በመቶዎችና በሽዎች በሚቆጠሩና ህዝብ ራሱ በፈጠራቸው ቡድኖች የሚመሩ እንቅስቃሴዎች፣ ለዘመናት የፖለቲካ ድርጅቶች ምንም ሊያደረጓቸው ያልቿላቸውን አምባገነኖች ሲያንበረክኩ አይተናል። ለነጻነት መምጣት ለሚጣደፍና አላማው ህዝብ የነጻነትና የስልጣን ባለቤት እንዲሆን ፍላጎት ላለው ድርጅት ከዚህ በላይ ሊያስቀና የሚችል ኩነት ከየትም ሊመጣ አይችልም።

በዚህ ጽሁፍ ተደጋግሞ እንደተገለጸው “ምክክር እናድርግ የምንለው ተሰባስበን ህዝብን እንምራ” ለማለት አይደለም። ተባብረን መምራት እንደማንችል ህዝቡ ስላዬ “ተባብረናል!” ብንለውም ቃላችንን በተግባር ደግፈን እስካላሳየነው አያምንም። በተለያዩ ሃገራት ያለፖለቲካ ድርጅቶች ተሳትፎ ህዝብ ትግሉን ራሱ በራሱ ለመምራት የተገደደው በድርጅቶች ድክመት መሆኑን እናውቃለን። የኢትዮጵያ ሁኔታ ደግሞ ከሌላው የባሰ ነው። እኛ ለራሳችን ከምንሰጠውና ግምትና ከምናስበው

በታች ነው ስለኛ ህዝብ ያለው ግምት። ከኛ የሚጠብቀው በጣም አነስተኛ ነገር ነው። ህዝባችን "ግፋበት እኛ ባለን አቅም ከጎንህ ነን። ለማሸነፍ የምትችለው አንድ ስትሆን ነው። የዘር፣ የሃይማኖት ልዩነትህን እያጎላ ከፍፍሎ እየገዛህ ያለውን ወያኔ አትስማ። ሁላችንም ለአባላታቾችንና ለደጋፊዎቻችን በሙሉ የህዝቡን የትግል አንድነት የሚጎዱ እርምጃዎች እንዳይወሰዱ በጋራ እንዲቆሙ ጥሪ እናቀርባለን። አንተ መስዋእትነት በምትከፍልበት ወቅት ስቃይህ መና ሊያደረጉ የሚችሉ ማናቸውንም ጎጂ እርምጃዎች ላለመውሰድ ቃል እንገባለን" እንድንለው ይፈልጋል። ።

ከዚህም አልፎ ህዝብ በራሱ ሃይል ፈንቅሎ በሚወጣበት ወቅት የተሻለ አጋር እንድንሆነው ይሻል። መሪ እንድንሆነው አይደለም፤ አጋር እንድንሆነው ይሻል። ይህን ሃላፊነት ለመወጣት "በጋራ የህዝብን ጥያቄ ማስተጋባት የምንችልበትን፤ በጋራ ድጋፍ ልናደርግለት የምችልበትን ቀላል የሆነ ያልተወሳሰበ መዋቅራዊ ቅርጽ ያለው አሰራር ፈጥረን እንገኝ" ነው የምንለው። ይህ መዋቅር በዚህ ጽሁፍ መግቢያ ላይ ከጠቀስነው የትብብርና የህብረት ምስረታ የተለየ ነው። ግልጽ የሆነ ተጨባጭና ሊሰራ በሚችል ተግባር ላይ ያተኮረ ነው። በተግባር ላይ ባተኮረ ጉዳይ ላይ የሚደረግ የመመካከርና የመተባበር ጅማሮ ከጊዚያዊና ወቅታዊ ጉዳዮች ባሻገር ሊኖር የሚገባውን ስፋትና ጥልቀት ያላቸውን ጥያቄዎች አንስቶ ለመነጋገር ሁኔታወን ያመቻቻል። ውለው አድረው በሂደት ሊፈቱ ወይም ሂደቱ ጠርጎ የሚያወስዳቸውን ጥያቄዎች ያለወቅቱና ያለቦታው በማቅረብ ትንሹንም ስራ በጋራ ለመስራት እንዳንችል ያደረጉንን ደንቃራዎች ይጠርጋል።

## 7. በህዝብ ፍላጎት የሚዘወር የትብብር ጥሪና መስፈርቶቹ

ባሁኑ ወቅት ተባብረን እንስራ ወይም ተባብራችሁ ስሩ የሚለውን ጥሪ የሚገፋው ከየትኛውም ቡድን ድርጅታዊ አጀንዳና ፓሊሲ ውጪ የቆመ የራሱ ህይወት ያለው ጉዳይ ነው። የሃገሪቱ ህዝብ ከድርጅቶች ቁጥጥር ውጭ ለአመጽ እየተንተከተከ ያለበት ሁኔታ ነው። ይህ አመጽ ለሙብትና ለነጻነት መከበር ከግፍና ሰቆቃ ለመገላገል የሚቀሰቀስ ነው። ይህ አመጽ በድርጅቶች የሚመራና ድርጅቶች ከዚህ ቀደም በሃገራችን እንዳደረጉት አንድን ድርጅት ወይም የድርጅት መሪ ለማንገስ ያለመ አይደለም። በመሆኑም ሁላችንንም ለራሳችን ማቅረብ የሚገባ ጥያቄ አንድ ነገር ላይ ብቻ የሚያጠነጥን ነው።

- በተደራጀ መንገድ የምንንቀሳቀሰውን የፖለቲካ ድርጅቶችን ሳይቀር ለመቆጣጠር የሚችል የህዝብ የበላይነት ገና ከሂደቱ የነገሰበት ህዝባዊ የነጻነት ትግል እንዲቀሰቀስ ከምር እንፈልጋለን?
- ለዚህ አላማ የሚነሳን ህዝብ እንደግፋለን?
- ይህ በህዝባዊ እምቢተኛነት የሚደረግ የነጻነት ትግል በተከፋፈለ ህብረተሰብ ውስጥ ሊሳካ አይችልም። ይህ የህዝብ አላማ እንዲሳካ ህዝብ በዘር በሃይማኖት በሌሎችም ጉዳዮች ሳይከፋፈል በአንድነት መነሳት ያስፈልገዋል ብለን እናምናለን? ይህን ተረድተን ሁላችንም ባለችን አቅም ህዝብ ባንድነት እንዲነሳ ጥሪ ለማድረግ ዝግጁ ነንን?

አዎን ህዝብ በአንድነት እንዲነሳ፣ የፖለቲካ እጣውን በጁ እንዲያስገባ ፣ ዴሞክራሲያዊ ስርአትን ለመፍጠር አልሞ እንዲነሳ ለመታግል ዝግጁ ነኝ የሚል ድርጅት፣ ይህንንም በተግባር ለማረጋገጥ ሃላፊነት እወስዳለሁ የሚል ድርጅት፣ ሌላ ምንም የሚጨመር የሚቀነስ የመተባበሪያ መስፈርት ሳያስፈልገው በሃገራችን ሰማይ ላይ እያስገመገመ ያለው የህዝባዊ እምቢኛነት ወዳጅ ሆኖ መታየት ይገባዋል። ከዚህም ሃይል ጋር በጋራ ለመስራት መቸገር ፈጽሞ የለብንም። በዚህ ከተስማማን ሌሎች ልዮነቶቻችን ህዝብ በአንድነት ተነስቶ በትግሉ እንዲፈጥረውና እንዲቆጣጠረው በጋር በታገልንለት የዲሞክራሲ ስርአት ይፈታል።

ባለንበት ወቅት "ህዝብ በአንድነት ለዲሞክራሲ መታገል አለበት" የሚል ሃይል፤ ይህንንም በተገኘው ሚድያ የሚያስተጋባ፣ በዲፕሎማሲ መድረኩ የሚሟገት፤ ለደጋፊዎቹና አባላቱ ተመሳሳይ መልእክት የሚያስተላላፍ እስከሆነ ድረስ፣ አንድ ድርጅት በድርጅታዊ ፕሮግራሙ የኮምኒስት ይሁን የካፒታሊስት ርእዮተ አለም ያራምድ፣ አሃዳዊ የሆነ መንግስታዊ አስተዳደር ወይም ፌደራላዊ አስተዳደር ከዛም አልፎ የመገንጠል አላማ ይኑረው፤ ለውጥ ለማምጣት ጠመንጃ አንግቦ ይንቀሳቀስ አይንቀሳቀስ፤ በመለስ ፈቃድ ህጋዊ እውቅና አግኝቶ ይንቀሳቀስ ወይም በመለስ ውሳኔ ህገ- ወጥ ይባል፤ ትንሽ ይሁን ትልቅ

የህዝባዊ አንድነትና የዴሞክራሲ ሃይሉ ጎራ ውስጥ ነው። ህዝብ በአንድነት ለዴሞክራሲ እንዲነሳና ሁሉንም ዜጎች፣ሁሉንም ማህበረሰቦችና ሁሉንም የፖለቲካ ድርጅቶች በእኩልነትና የሚያስተናግድ ዲሞክራሲያዊ ስርአት እንዲፈጥር መቀስቀስ እድሌን በዴሞክራሲያዊ ስርአት እሞክራለሁ ከማለት ሌላ ምን ትርጉም ሊሰጠው አይችልም። ዲሞክራሲን እራሱን ካልፈራነው በስተቀር ይህን አይነቱን ትብብር የምንፈራበት ምክንያት ሊኖር አይገባውም።

ከዚህ ቀደም የነበሩ የመተባበር ጥያቄዎች ሌሎችን የመተባበሪያ መስፈርቶች እንዲኖሩን የሚያስገድዱ ነበሩ። ወደፊትም ሌሎች የመተባበሪያ መስፈረቶችን የሚጠይቁ የተለዩ ወቅቶች ሊመጡ ይችላሉ። የመሰባሰቡን አጀንዳ እየገፋው ያለው በህዝብ የሚዘወረው በአንድነት ለዴሞክራሲ የሚደረግ የትግል ፍላጎት ሳይሆን ድርጅቶች አቅደው የሚመሩት የትግል ፍላጎት በሚሆንበት ወቅት ድርጅቶች የፈለጉትንና የሚስማማቸውን የመተባበሪያ መስፈርቶች ማስቀመጥ ይችላሉ።

የመገንጠል አላማ ያለው ቡድንና አላማው የመገንጠል መብት በስራ ላይ እንዲውል የሚፈልግ ከሌላ አካል የሚፈጥረውም ትብብር ይህንን የሚያሳካ እንዲሆንለት እንደሚፈልግ ግልጽ ነው። እንዲህ አይነቱ ቡድን እርሱ ያለበት ትብብር አካል ስለሚሆኑ ሃይሎች የሚያስቀምጠው መስፈርት “በመገንጠል መብት የሚያምኑና ለዚህ ጠንክረው የሚሰሩ” የሚል ይሆናል። በተመሳሳይም የኢትዮጵያ አንድነት ማስጠበቅ አላማው አድርጎ የሚነሳ የትብብር ምስረታ በኢትዮጵያ  አንድነት ላይ እምነት የሌላቸውን የሚያሰባስብበት ምክንያት ሊኖር አይገባውም። የመሰባሰቢያ  መስፈርቱ ትብብሩ ከቆመለት አላማ ጋር የተያያዘ ስለሆነ በአንድነት ማመን የግድ ነው።

በተለይ ባለፈው ወር በግንቦት7 በኩል ውስጥ ውስጡን ስንደክምበት የሰነበትነው የትብብር ጥሪ መነሻውም መድረሻውም ከዚህ በላይ ከተቀመጠው የተለየ ነው። የመተባበርን አጀንዳ  የሚገፉት ድርግቶች ሳይሆኑ የከባቢያችንና  የሃገራችን ሁኔታ ነው።  ዋናው የመተባበሪያው መስፈረት **ዲሞክራሲና ህዝባዊ አንድነት** ነው። ህዝብ በጋራና  በአንድነት መነሳት አለበት የሚል አቋም አለህ ወይ?  ህዝብ በአንድነት ሲነሳ በሃገሪቱ ዲሞክራሲያው ስርአት ለማንገስ መሆን ይገባዋል የሚለውን ሃሳብ ትደግፋለህ ወይ? ለሁለቱ ጥያቄዎች አዎንታዊ መልስ ከሰጠን ከማንኛውም ሃይል ጋር ለመስራት የምንቸገርበት ምክንያት ሊኖር አይገባም በማለት ተንቀሳቅሰናል። ያለንበት ዘመን፣  ህዝብን ማእከል ያደረገው  የስርአት ለውጥ እንቅስቃሴ አዲስ የትብብር ፓራዳይም ይዞልን መጥቷል።  ይህ አዲስ ፓራዳይም በህዝብና  በድርጅቶች መሃከል ያለውን ግንኙነት በተመሪና  በመሪ መሃል ያለ ግንኙነት መሆኑ ቀረቶ ድርጅቶችን ከአጋርነት ያለፈ ቦታ አይሰጣቸውም። ያም ቢሆን ለዴሞክራሲ የቆሙትን ድርጅቶች ብቻ  ነው።  ይህ አዲስ የትብብር ፓራዳይም ይዞት የመጣው ትብብር ህዝብ አንገቱን ደፍቶ  በነበረበት ወቅት፣ የፖለቲካ ድርጅቶች ከህዝብ ጀርባ  መከረው፣ ራሳቸው ቀስቃሽና  መሪ ሆነው፣ እንደተለመደው በህዝብ ፍላጎት ሳይሆን በራሳቸው ፍላጎት ስለሚቀርጹት መንግስታዊ ስርአት ለመወሰን የሚጠሩት ትብብር ትልቅ ልዩነት አላቸው።

በህዝብ ፍላጎትና ግፊት የሚዘወረው ትብብር ባነስተኛ መግባባት መከናወን የሚችል ትብብር ነው። የትብብሩ ገዥ ሃይል ህዝብ በመሆኑ ዴሞክራሲያዊ ከሆነ ሂደት ውጭ የራሱን ፍላጎት ለማስፈጸም የሚነሳንና የህዝቡን አንድነትና  ዴሞክራሲያዊ ፍላጎት ለማደናቀፍ የሚፈልግን የትኛውንም ሃይል የመቋቋም ጉልበት አለው። በተጨባጭ በተለያዩ  ሃገሮችም በስራ ላይ ሲውል ያየነው ነው። በኢትዮጵያም ዘመኑ ረዝሞ  እረስተነው ካልሆነ የ1966ቱ አብዮት ሲፈነዳ ከመቼውም ጊዜ በላቀ ደረጃ  የሃገሪቱን የተለያዩ እምነቶች፣ ዘውጌ ማህበረሰባት በአንድነት የያዘ ነበር። የበለጠ ያጠናከረም ነበር።  ለእስልምና እምነት ተከታዮች መብት መከበር ክርስቲያኑ ሰልፍ ወጥቶ ነበር። የመሬት ላራሹን ፍትሃዊ ጥያቄ፣ የሰፋፊ ባለመሬት ባለቤቶች የተማሩ ልጆች ብቻ ሳይሆኑ ከባለመሬቶቹ ወላጆቻቸውም ጭምር እርምጃው ሃገርን ከኋላቀረነት ያላቅቃል በሚል እምነት ድጋፋቸው የሰጡት በርካቶች ነበሩ። የብሄር ብሄረሰቦች መብት እንዲከበር የነበረው ጥያቄ ህብረተሰባችን የከፋፋፈለ አልነበረም። ህዝብ ከፖ ለቲካ ድርጅቶች ቁጥጥር ውጭ ራሱ በግብታዊነት የተነሳባቸው የ1966ቶቹ የመጀመሪያዎቹ የአብዮቱ ወቅቶች ህብረተሰቡን የበለጠ ያቀራረቡ እንጂ ህብረተሰቡን የበታተኑ አልነበሩም። የድርጅቶች እጅ መብዛትና ህዝብ ከፖለቲካ መድረኩ የተገፋበት አፋኝ መንግስታዊ ስርአት መጠናከር ሲጀምር ነው የአብዮቱ ቃና መጎርናት የጀመረው።

ምርጫ 1997 ህዝብ በምርጫው ወቅት ያሳየው ዲሲፕሊንና ሰላማዊነት በደንብ በተደራጁ ፓርቲዎች መሪነት የመጣ አልነበረም። በተመሳሳይም ህዝብ ሚያዝያ 30 1997 ቀን በመስቀል አደባባይ ያደረገው ሰልፍ በቅንጅት ይጠራ እንጂ በቅንጅት የተደራጀና የተመራ አልነበረም። ያንን ለማድረግም ቅንጅት በአዲስ አበባ ውስጥ ድርጅታዊ መዋቅሩና መረቡ እንዳልነበረው በቦታው የነበረን እናውቃለን። የድርጅቶች ይሁን የመንግስት የጸጥታ አስጠባቂ ሃይሎች በሌሉበት ሁኔታ በዚህ ታላቅ ትእይንተ ህዝብ ወቅት የታየው ሰላም ህዝቡ ከውስጡ ከሚፈልቀው ቀናነት፣ ስልጥኑነትና አርቆ አሳቢነት የመጣ እንጂ በድርጅቶች ተቆጣጣሪነት የመጣ አልነበረም።

ህዝብ ያለ ድርጅቶች መሪነት ቢነሳ ለሃገሪቱ አደገኛ ነው በማለት ከሩቁ ሆነው ለሚጮሁት መልሳችን "1997 እኮ እሩቅ አይደለም። ዘረኛው የወያኔ መርዝ ያኔም ተዘረቶ ነበር። በዛ መርዝ አብዶ የተነሳ እብድ ህዝብ ግን አልታየም።" የሚል ነው። ዛሬም ቢሆን ወያኔ የዘራው የከፋፋይነት መርዝ የፈለገውን ያህል አደገኛ ቢሆን ይህን መርዝ መንቀል ለኢትዮጵያ ህዝብ የሚያዳግተው አይደለም። ህዝብ በጋራ የቀመሰው ግፍና ስቃይ ይህን መርዝ በአንድነት ነቅሎ በአንድነት ግፍና ሰቆቃ እንዲያበቃ መነሳት እንዳለበት አስተምሮታል። መጪው ህዝባዊ እምቢተኛነት ይህን የህዝባዊ አንድነት ባህርዩን ጠብቆ ለምን መዝለቅ እንደሚገባው ለ20 አመት በጥቂት ዘረኞች እጅ ወደቆ አበሳውን ያየው በመሬቱ ላይ የሚኖረው ብዙሃኑ የሃገሪቱ ዜጋ ያውቀዋል። የወያኔ ጥንካሬ ዜጎችንና ማህበረሰቦችን እንዲሁም የፖለቲካ ድርጅቶችን መከፋፈል በማቻሉ እንጂ እንኳን 20 አመት አንድም አመት ስልጣን ላይ ሊቆይ የማይችል የጥቂት ዘረኞችና ዘራፊዎች ቡድን እንደሆነ ለሁሉም ፍንትው ብሎ የተያ ሃቅ ሆኗል። በዚህ ላይ መጪው ህዝባዊ እምቢተኛነት ይዞት የሚነሳውን የዴሞክራሲና የአንድነት ህዝባዊ ባህርዩን እንዲጠብቅ ድርጅቶች ድጋፋቸውን ካከሉበትና ህዝብም ለድርጅቶች ቅብጠት ልጓም ማበጀት እስከቻለ፤ አዲሱ አብዮት የሰነቀውን የህዝብና የሃገር ብሩህ ተስፋ እውን የማያደረግበት ምክንያት አይኖርም። ድርጅቶች ህዝብን አምነው የህዝብ ትግልን ለመደገፍ በጋራ ለመስራት የተለያዩ ሰበቦች መደረደር አያስፈልጋቸውም የምንለውም ለዚህ ነው።

ከዚህ ውጭ ያለው ለብዙ ግዜ ስንሞክረው የቆየነው ትብብር በባህርይው መሰረታዊ የሆኑ የድርጅቶች የአቋሞች መሸጋሸግ ሳይደረግ የሚከናወን አይደለም። ይህ ደግሞ በቀላሉ ሊሆን እንደማይችል ከአመታት ተመክሮአችን የተገነዘብነው ነው። መሰረታዊ የሆነ የአቋም መሸጋገሸግ ሳያስፈልጋቸው መሰባሰብ የሚችሉ ድርጅቶች ስለሚያደርጉት ትብብር ወይም ግንባር ከሆነ የምናወራው እርባናው ብዙም አይታየንም። የሚቀራረቡ እምነቶች ያላቸው ድርጅቶች ትብብር ስልጣን ላይ ያለው መንግስትና የሃገሪቱ ልሂቅ የሰነጣጠሩትን ማህበረሰብ የሚያቀራርብና ከራሱ ጋር የታረቀ ማህበረሰብ ለመፍጠር የሚኖረው አስተዋጽኦዋ አነስተኛ ነው። እንዲህ ብለንም እንዲህ አይነቱ ትብብር መፈጠር የለበትም የሚል እምነት ግንቦት7 የለውም። እንዲህ አይነቱ ትብብር ሲፈጠር የራሱ ጥንቃቄዎች ሊኖሩት ይገባል።በዚህ መንገድ የምንሄደው የሃገሪቱ ልሂቅ በተለያዩ ጎራዎች ተከፋፍሎ ለሚገባበት ግጭት ሃይል ለማሰባሰብና ዝግጅት ለማድረግ ከሆነ የውድመት ኢላማ ያለው ትብብር ከመሆን አይዘልም። ይህ በጎራ ተከፋፍሎ የሚደረግ ንትርክና ግጭት ደግሞ ሞክረነው፣ ሞክረነው ከውርደትና ድህነት አዙሪት ውስጥ እንዳንወጣ አድርጎ ያኖረን አሮጌ አስተሳሰብ ነው። ራሳቸውን በጸረ ወያኔ ጎራ የሚመድቡ በዚህም ጎራ ውስጥ ለመሆናቸው እኛም ጥርጣሬ የሌለን አንዳንድ ቡድኖችና ግለሰቦች በየድረ ገጹ የሚያሰራጩት ጽሁፍ አሁንም ወደእዛው ("እኛ" እና "እነሱ" ወደሚል አንዱ አሸናፊ ሌላውን ተሸናፊ ወደሚያደረግ) አሰራር ለመግባት እንድንጣደፍ የሚገፋፉ ናቸው? እኛ ከዚህ የተሻለ አማራጭ አለ ባዮች ነን። በአንድነት ለዴሞክራሲ ለመነሳት እየተንጠራራ ያለን ህዝብ የትግል አንድነቱንና የዲሞክራሲ ህልሙ እንዲሳካ ለማገዝ ከምር መተባበር። ይህ ትብብርም ሁሉን ያቀፈ እንዲሆን መጣር።

## 8. ማሳረጊያ

የዘመኑ የመረጃ ቴክኖሎጂ መጥቶ ከልሂቁ ጀርባ ተራውን ህዝብ እርስ በርሱ የሚነጋገርበት ሁኔታ ፈጥሮ በጣህሂር አደባባይ የተመለከትነው በህዝብ የተሰራ ታሪክ እስከሚያሳየን ድረስ አንዳንዶቻችን "ታሪክ ሰሪው ህዝብ ነው" የሚለውን የቆየ አባባል፣ ህዝብን በኩሊነት እየተገለገሉ ያሻቸውን ሲያሰሩት የኖሩ አምባገነን ብልጣብልጦች አባባል አድርገነው ወስደነው ነበር። ከመሃከላችንም "ህዝብ ታሪክ ይሰራል፤ እውነት ነው። የሚሰራው ግን በተራ ኩሊነት ነው። ዋናው መሃንዲስና አርክቴክት ልሂቁ ነው" በማለት የጻፉት ጽሁፍ ቀለሙ ያልደረቀላቸውም እናገኛለን። ሁላችንም ግን በጣህሂር አደባባይ

ህዝብ ታሪክ ሰሪነቱን ሲያስመክር አየን። አንዳንዶቻችን በህዝብ ላይ መያዝ ጀምረነው የነበረው ጥርጣሬ የሚያስተዛዝብ እንደሆነ ተገነዘብን። ህይወት ማለቂያ የሌለው ትምርት የሚሰጥበት ኮሌጅ ነውና እድሜ ከሰጠን ገና ብዙ እንማራለን።

የተሳሳተና መታረም የሚገባው አመለካከት ተሸካሚ ከመሆን ስህተታችን እያረምንና በአደባባይ እየተናገርን የራሳችንና የሌሎችም የትዝብ ኢላማ መሆን ይሻላል። ሃገር ወገን የምንላቸውና ከኛ የግል ስም፣ ጥቅምና ክብር በላይ ናቸው ብለን ለምናቀርባቸው ክቡር ነገሮች ስንል፣ ለመታረምና ለመስተካከል ድፍረቱ ይኑረን። ለመመካከር ለመተባበር ምንም አይነት ችግር በሌለበት ባሁኑ ወቅት ተባብረን መስራት በሚገባን ሃይሎች መሃከል ተጨባጭነት የሌላቸውን ጉዳዮች እየሰነቀሩ ወያኔን እረስተን ወደ እርስ በርስ ንትርክ እንድንመለስ በጥቂቶች የሚሰጠነን ፈተና ተሻግረን ወደፊት እንጓዝ። ሁሉም የቻለው ይስራ። ሁሉም በዋናው የሃገር ጠለት በመለስ ዜናዊ ላይ ያነጣጥር። ሁሉም “ህዝብ የሚበጀውን ያውቃል” ለሚለው አመለካከት ተገዢ ይሁን። ሁሉም በህዝብ ለመዳኘት ፈቃደኛ ይሁን። በዚህ ቀውጢ ሰአት፤ የሀገሪቱ ወጣትና ህዝብ የምንችለውን ድጋፍ እንድናደረግለት በሚጠይቅበት ሰአት፤ ድጋፍ ለማድረግ ብቃቱና ክህሎቱ ባይኖረንም ይህን ለማድረግ ደፋ ቀና የሚሉትን ክፍሎች አናደናቅፍ። በአንዳንድ ሁኔታዎች ምንም አለመስራት ራሱን የቻለ አስተዋጿኦ ይኖረዋል። ምንም ባለመስራታችን አስተዋጾኦችን ከታየ ባለመስራታችን ልናፍር አይገባም።